በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

የልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት

የፕራይቬታይዜሽን ክፍያ አሰባሰብ መመሪያ

515/2013

ጳጉሜ 2008

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

የልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት የፕራይቬታይዜሽን

ክፍያ አሰባሰብ መመሪያ

515/2013

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች የመንግስት የልማት ድርጅቶችን/አክሲዮን ማህበራትን ወደ ግል አልሚዎች በማዛወር ውጤታማ ሥራ እያከናወነ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ከፕራቬታይዜሽን ፕሮግራም ጋር የተያያዙ የተለያዩ ክፍያዎችን በቅልጥፍና በግልጽነትና ተጠያቅነት በሰፈነበት አሠራር ለመሰብሰብ የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተለይ ድርጅቶቹ ወደ ግል አልሚዎች የሚተላለፉት በውል ላይ ተመስርቶ በሙሉ ክፍያ ወይም በተራዘመ ክፍያ /deffered payment/ በመሆኑ የሽያጭ ክፍያውንም ሆነ የርክክብ ልዩነት ትመና ክፍያ በተቀላጠፈና በግልጽ አሠራር ለመሰብሰብ እንዲቻል በመመሪያ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በመንግስት እጅ የነበሩ አክሲዮን ማህበራት ወደ ግል አልሚዎች ከመተላለፋቸው በፊት በተለያዩ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች እንዲሁም የሚያጋጥማቸውን የስራ ማስኬጃ ችግር ለማቃለል ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በውል ላይ የተመሰረተ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግ በመሆኑ እንዲሁም ባተረፉት መጠን የመንግስት ትርፍ ድርሻ የሚከፍሉ የሚደረግ በመሆኑ ድርጅቶቹ የተበደሩትን ክፍያ እና የነበረባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ሳያጠናቅቁ ወደ ግል አልሚዎች በሚዛወሩበት ወቅት ያለባቸውን እዳ ገገርው እንዲከፍል በውለታ ሰነዱ እንዲካተት የሚደረግ በመሆኑ የክፍያውን አሰባሰብ በግልጽ ማስቀመጥ አስፈለጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916 /2008 አንቀጽ 31 (1)(ለ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ ፕራይቬታይዜሽን ክፍያ አሳባሰብ መመሪያ ቁ 515/2013 ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. "ፕራይቬታይዜሽን" ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ለማዛወር በወጣው" አዋጅ ቁጥር146 /1991 አንቀጽ 2/1 መሰረት የተሰጠው ትርጓሜ ይኖራዋል፤

2.2. "ክፍያ" ማለት ከልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት ሽያጭ፣ የሊዝ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር፣ የርክክብ ልዩነት ዋጋ ትመና እና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያዎችን ያጠቃልላል፤

2.3. "የመንግስት የልማት ድርጅት" ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀጽ 2 (5) መሰረት የተሰጠው ትርጓሜ ይኖራዋል፤

2.4. "አክሲዮን ማህበር" ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዘ ወይም በመንግሥትና በግል በጋራ የተያዘ አክሲዮን ማህበር ማለት ነው፡፡

2.5. "የመንግሥት የአክሲዮን ድርሻ" ማለት በከፊል በመንግስት ባለቤትነት በተያዘ አክሲዮን ማህበር ውስጥ ያለ የመንግሥት አክሲዮን መጠን ነው፡፡

2.6. "ቅድሚያ ክፍያ" ማለት ገገርዎች በፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ለሚገዟቸው የልማት ድርጅቶች ወይም የመንግሥት አክሲዮን ድርሻ ውለታ ከመፈረማቸው በፊት በቅድሚያ ገቢ የሚያደርጉት ክፍያ ማለት ነው፡፡

2.7. "ሙሉ ክፍያ" ማለት ገዢዎች በፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ለሚገዟቸው የልማት ድርጅቶች ወይም የመንግሥት አክሲዮን ድርሻ የሚከፍሉት ሙሉ ክፍያ ማለት ነው፡፡

2.8. "የተራዘመ ክፍያ /Deferred Payment/" ማለት ገገርዎች በፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ለሚሸጡ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት በውለታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ቅድሚያ ክፍያውን ከፈፀሙ በኂላ በተወሰኑ ዓመታት የሚያጠናቅቁት ቀሪ ክፍያ ማለት ነው፡፡

2.9. "የሽያጭ ውል" ማለት በሽያጭ የሚተላለፉ የልማት ድርጅቶች ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅሞችን እንዲሁም ግዴታዎችን በተመለከተ ሻጭ እና ገዢ ተስማምተው የሚፈራረሙበት የስምምነት ሰነድ ነው።

2.10. "ዓመታዊ የሽያጭ ክፍያ" ማለት ገዢ በውሉ መሰረት በዓመት ለመክፈል የተስማማው የክፍያ መጠን ነው፡

2.11. "በወቅቱ ያልተከፈለ ቀሪ ክፍያ" ማለት ገዢ በውሉ መሰረት በዓመት ለመክፈል በተስማማው የክፍያ ቀን ያልከፈለው የክፍያ መጠን ነው።

2.12. "ቀሪ ክፍያ" ማለት ገዢ ከገዛው ድርጅት የመሸጫ ዋጋው ውስጥ ለዋናው፣ ለወለድ እና ለቅጣት የተወሰነ ክፍያ ፈጽሞ የሚቀርበት እዳ ማለት ነው፡

2.13. "እኩል ዓመታዊ ክፍያ" ማለት ገዢ በውሉታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ቅድሚያ ክፍያውን ፈጽሞ ቀሪው ክፍያ ለቀሪዎቹ ዓመታት በእኩል ተካፍሎ በየዓመቱ እንዲከፍል የሚጠበቅበት መጠን ማለት ነው።

2.14. "ዓመት" ማለት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ጳጉሜን ጨምሮ በውል ስምምነቱ መሠረት ዓመታዊ ወለድንና ቅጣትን ለማስላት ሥራ ላይ የሚውለው 365 ቀናት ማለት ነው።

2.15. "የርክክብ ልዩነት ክፍያ" ማለት ገዢዎች ቅድሚያ ክፍያ ወይም ሙሉ ክፍያ ፈጽመው ድርጅቱን ወይም አ/ማህበሩን በሚረከቡበት ወቅት በትመና ላይ ያልተካተቱ እና በርክክብ ወቅት የተገኙ ንብረቶችን ዋጋ ትመና ተደርጎ ውሉን መሰረት በማድረግ ገዢዎች የሚከፍሉት ክፍያ ማለት ነው።

2.16. "የሊዝ ውል" ማለት በሊዝ ከሚተላለፉ ድርጅቶች ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅሞችን እንዲሁም ግዴታዎችን በተመለከተ አከራይና ተከራይ ተስማምተው የሚፈራረሙበት የስምምነት ሰነድ ነው።

2.17. "የሊዝ ክፍያ" ማለት ተከራይ በውሉ መሰረት ለመክፈል የተስማማው የክፍያ መጠን ነው።

2.18. "የማስቀመጫ ወለድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ለተቀማጭ ገንዘብ በየጊዜው የሚያወጣው የተቀማጭ ገንዘብ የወለድ ምጣኔ ማለት ነው።

2.19. "የማበደሪያ ወለድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በየጊዜው የሚያወጣው የገንዘብ ማበደሪያ የወለድ ምጣኔ ማለት ነው።

2.20. "አማካይ የማበደሪያ ወለድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በተወሰነ ወቅት የሚያወጣው የከፍተኛውና የዝቅተኛው የገንዘብ የማበደሪያ የወለድ ምጣኔ አማካይ ማለት ነው፡፡

2.21. "ቅጣት" ማለት ገዢዎች በውለታ ሰነዱ መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ የሚታሰብ አማካይ የባንክ የማበደሪያ የወለድ ምጣኔ ላይ የሚጨመር 1% ክፍያ ማለት ነው፡፡

2.22. "የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር" ማለት በመንግስት እጅ የሚገኙ የልማት ድርጅቶች/አክስዮን ማህበራት ለተለያዩ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች እና ለሚያጋጥማቸው የስራ ማስኬጃ እጥረት የሚውል ከየኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚያገኙት በውለታ ላይ የተመሰረተ ብድር ነው፡፡

2.23. "የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ" ማለት" የመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 2 (9) መሰረት የተሰጠው ትርጓሜ ይኖራዋል፤

2.24. "የመንግስት የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ" ማለት መንግስት በአክሲዮን ማህበራት ውስጥ የሚኖረውን የመንግስት ድርሻ በሽያጭ ለገዢዎች ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡

3.የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማናቸውም የመንግስት ልማት ድርጅቶች/ አክሲዮን ማህበራት የፕራይቬታይዜሽን ክፍያ አሳባሰብ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

4. የልማት ድርጅቶች፣ አክሲዮን ማህበራት ሽያጭ እና ወለድ ክፍያ መርሆዎች

4.1. ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች

ሀ. ሙሉ ክፍያ የሚፈጽሙ ገዢዎች ውል ከመፈረሙ በፊት የመሸጫ ዋጋውን ቢያንስ 30% በቅድሚያ ከፍለው ቀሪውን ሙሉ በሙሉ ርክክቡ ከመጠናቀቁ በፊት ባሉት 5 የስራ ቀናት ውስጥ አስቀድመው ከፍለው ያጠናቅቃሉ፡፡

ለ. የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን የካፒታል አቅም ውስንነት ከግንዛቤ በማስገባት የአገር ውስጥ ባለሃብቶች የሽያጭ ውል ከመፈረሙ በፊት ከድርጅቱ የመሸጫ

ዋጋ ቢያንስ 35% ቅድሚያ ይከፍላሉ። ቀሪውን 65% እስከ 5 ዓመት በተከታታይ እኩል ዓመታዊ ክፍያ በመክፈል ያጠናቅቃሉ።

ሐ. ባልተፈጸመ ቀሪ ክፍያ ላይ ገዢው የባንክ የማስቀመጫ ወለድ ተመን መሰረት ወለድ ይከፍልበታል።

ሠ. ክፍያውን በወቅቱ ሳይፈጽም የቀረ ገዢ በባንክ አማካይ የማበደሪያ ወለድ ላይ 1% ቅጣት ታክሎበት እንዲከፍል ይደረጋል።

ረ. የክፍያ የጊዜ ገደብ ማራዘምን በተመለከተ በተለየ ሁኔታ በመንግስት ውሳኔ ከተሰጠ በውሳኔው መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

4.2. ለውጭ አገር ባለሃብቶች

ሀ. ሙሉ ክፍያ የሚፈጽሙ የዉጭ ሀገር ገዢዎች ውል ከመፈረሙ በፊት የመሸጫ ዋጋውን ቢያንስ 50% በቅድሚያ ክፍለው ቀሪውን ሙሉ በሙሉ ርክክቡ ከመጠናቀቁ በፊት ባሉት 5 የስራ ቀናት ውስጥ አስቀድመው ከፍለው ያጠናቅቃሉ።

ለ. የውጭ አገር ባለብቶች በተራዘመ የክፍያ አሰራር ተጠቃሚ የሚሆኑት ከዚህ ቀደም በሃገር ውስጥ በተመሳሳይ ወይም በሌላ መስክ ያካሄዱት ኢንቨስትመንት እና ያስገኙት ውጤት፣የገዢው ኩባንያ ህጋዊ አቋም፣ የሚሸጠው ድርጅት ዋጋ ከ5 ሚሊዮን ዶላር ያላነሰ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ይሆናል። የውጭ ሃገር ባለሃብቶች ክፍያ የሚፈጽሙት በብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው የውጭ ሃገር ገንዘብ ይሆናል።

ሐ. ገዢው ውለታ ከመፈረሙ በፊት ቢያንስ 50% ክፍሎ ቀሪውን 50% እስከ 3 ዓመታት በእኩል ዓመታዊ ክፍያ ከፍሉ ማጠናቀቅ አለበት።

መ. ባልተፈጸመ ቀሪ ክፍያ ላይ ገዢው የባንክ የማስቀመጫ ወለድ ተመን መሰረት ወለድ ይከፍልበታል።

ሠ. ገዢው ክፍያውን በወቅቱ ሳይፈጸም ከቀረ በባንክ አማካይ የማበደሪያ ወለድ ላይ 1% ቅጣት ታክሎበት እንዲከፍል ይደረጋል።

ረ. የክፍያ የጊዜ ገደብ ማራዘምን በተመለከተ በተለየ ሁኔታ በመንግስት ውሳኔ ከተሰጠ ብቻ በውሳኔው መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

ክፍል ሶስት

5. የክፍያዎች፣ የወለድ እና ቅጣት አሰላል

5.1. በውል ስምምነቱ መሠረት ዓመታዊ ወለድንና ቅጣትን ለማስላት ሥራ ላይ የሚውለው የቀናት ብዛት 365 ይሆናል።

5.2. ለእያንዳንዱ በተራዘመ ክፍያ ለተዛወረ የልማት ድርጅት ዋናውን ገንዘብ፣ የተፈጸመ ክፍያ ፣ ቅጣትንና ወለድን እንዲሁም ቀሪ ክፍያ የሚያሳይ የሂሳብ ሌጀር ከፍቶ ሂሳቡንም አስልቶ በየወሩ በሃርድና በሶፍት ኮፒዎች በፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት እንዲያዝ ይደረጋል።

5.3. አንድ የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮን ማህበር ወይም የመንግስት አክሲዮን ድርሻ ለውጭ ባለሃብት ወይም ኩባንያ ሲሸጥ ወለድም ሆነ ቅጣት የሚሰላው በውል ስምምነቱ በተቀመጠው የወለድ ተመን መሠረት ነው። እንደዚሁም መከፈል ባለበት የውጪ ምንዛሪ ይሆናል።

5.4. በሽያጭ ውል ስምምነቱ ለወለድ ማስሊያነት የሚያዘው የማበደሪያ ወለድ ተመን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አማካይ የወለድ ምጣኔ መሠረት ያደረገ ሲሆን የማስቀመጫ ወለድ ምጣኔ ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣው የማስቀመጫ ወለድ ተመን መሠረት ይሆናል። ስለዚህም የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በየሦስት ወሩ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስቀመጫ እና የማበደሪያ ወለድ ተመን የሚያሳይ መረጃ በመሰብሰብ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል።

5.5. አንድ ባለዕዳ የመክፈያ ጊዜው ሳይደርስ ክፍያ ለመፈፀም ሲመጣ ወለድ የሚሰላው ክፍያ ለመፈጸም ከመጣበት ቀድሞ እስካለው ቀን ጊዜ ሆኖ ክፍያ የተፈጸመበት እለት ወለድ ወደሚቀጥለው ክፍያ ወቅት እንዲካተት ይደረጋል።

5.6. አንድ ባለዕዳ በመክፈያው ቀን ወይም ከመክፈያው ቀን በኋላ መክፈል ከሚገባው የገንዘብ መጠን በታች ይዞ ቢመጣ ባመጣው ገንዘብ ልክ ደረሰኝ ተቆርጦ ሂሳቡ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ነገር ግን ዕዳው በተሟላ መልኩ አለመከፈሉን እንዲሁም የዚህ ውጤት ምን እነደሆነ ለባለዕዳው በወቅቱ የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ አለበት፡፡

5.7. ቀድሞ በውል በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ቀሪ ክፍያ ላይ ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ርክክብ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

5.8. ገዢዎች ክፍያውን እራሳቸው በባንክ ገቢ ካደረጉ በኋላ በተለያየ ምክንያት የባንክ አድቫይሱን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በወቅቱ ማቅረብ ባይችሉ እና ዘግይተው ቢመጡ ወለድና ቅጣት የሚታሰበው ገንዘቡ በባንክ ገቢ በተደረገበት ቀን መሰረት ይሆናል፡፡

5.9. ቀደም ሲል ሂሳባቸውን አጠናቀዋል ተብለው ማስረጃ የተሰጣቸውና ሂሳቡ ኦዲት ሲደረግ ወይም በማንኛውም መንገድ ቀሪ እዳ እንዳለባቸው የተረጋገጠባቸው ቀሪ እዳውን እንዲከፍሉ በደብዳቤ ከተገለጸላቸው እለት ጀምሮ ባሉት 40 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ሊከፍሉ ይገባል፡፡ ሆኖም በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልከፈሉ ሳይከፍሉ ለቆዩበት ጊዜ በወቅቱ አማካይ የማበደሪያ ወለድ ተመን ላይ በተጨማሪ 1% ቅጣት ታክሎበት እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

5.10. የሽያጭ ውል እና ማሻሻያ ኮፒ እንደዚሁም የርክክብ ልዩነት ትመና ዋጋ በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ አማካኝነት ለኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት፣ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት፣ ለሕግ ዳይሬክቶሬት፣ ለኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ለመዝገብ ቤት ሁልጊዜም በወቅቱ መሰጠት አለበት፡፡

5.11. ከፋዮች ክፍያ ለመፈጸም በሚመጡበት ወቅት ካመጡት ገንዘብ ላይ መጀመሪያ ቅጣቱ እና ወለዱ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ለዋናው እዳ ክፍያ እንዲውል ይደረጋል፡፡

6. የርክክብ ልዩነት ሂሳብ አሰባሰብና የወለድ አሰላል

6.1. የርክክብ ልዩነት ትመና ተሰርቶ በሚኒስትሯ/ሩ ውሳኔ ካገኘ በኋላ የርክክብ ልዩነቱ እንዴትና በምን ያህል ጊዜ መከፈል እንዳለበት የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ በደብዳቤ ለገዢው አሳውቆ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት፣ ለህግ ዳይሬቶሬት፣ ለኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት እና ለሪኮርድና ዶክመንቴሽን አገልግሎት በግልባጭ ያሳውቃል።

6.2. የርክክብ ልዩነት ክፍያ እንዲፈጽሙ ለገዢዎች በደብዳቤ ከደረሳቸው 3ኛ የሥራ ቀን ጀምሮ ከዋናው የሽያጭ ቀሪ እዳ ጋር ተዳምሮ በቀሪዎቹ የክፍያ ጊዜያት በእኩል ክፍያ የሚከፈል ይሆናል ። ሆኖም በውሉ መሰረት ካልተከፈለ ወለድና ቅጣት እየታሰበበት የሚከፈል ይሆናል ።

6.3. የሽያጭ ዋጋውን ሙሉ ክፍያ ከፍለው ድርጅት የሚረከቡ ገዢዎች የርክክብ ልዩነት ትመና እንዲከፍሉ በደብዳቤ ከተገለጸላቸው በኋላ ባሉት 40 ቀናት ውስጥ ክፍያ እንዲፈጽሙ ይደረጋል። ሆኖም በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልከፈሉ ሳይከፍሉ ለቆዩበት ጊዜ በወቅቱ አማካይ የባንክ የማበደሪያ ወለድ ተመን ላይ በተጨማሪ 1% ቅጣት ታክሎበት እንዲከፍሉ ይደረጋል።

ክፍል አራት

7. የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር እና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ አሰባሰብ ዝርዝር አሰራር

7.1. የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ስርዓት ዳይሬክቶሬት በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ አማካይነት ወደ ግል የሚተላለፉት የልማት ድርጅቶች እና አክሲዮኖች አክሲዮኖች አስተዳደር ዘርፍ አማካይነት ወደ ግል ባለሃብት እስከሚዛወሩበት ወቅት የነበረባቸውን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድርና የመንግስት ትርፍ ድርሻ በተመለከተ የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት መነሻ በማድረግ መረጃውን የሽያጭ ውሉ ከመፈረሙ በፊት በውሉ ላይ መካተት እንዲችል ለህግ ዳይሬክቶርት፣ ለኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት እና ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ማስተላለፍ አለበት።

7.2. የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ስርዓት ዳይሬክቶሬት ወደ ግል የተላለፉ የልማት ድርጅቶች ወይም የአክሲዮን ማህበራትን የመንግስት ትርፍ ድርሻ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ እና የሂሳብ ሰነዶችን የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ያስተላልፋል።

7.3. የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ሰነዶችን መሰረት በማድረግ ተገቢውን ምዝገባ በማከናወን የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ እዳ ክፍያ በየወቅቱ የሚፈጽሙ ገዢዎች በሚያቀርቡት የባንክ ዲፖዚት እስሊፕ መሰረት ገንዘቡ ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ የገቢ ደረሰኝ ቆርጦ ይሰጣል።

7.4. የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ወደ ግል የተዛወሩ የልማት ድርጅቶች ወይም አክሲዮን ማህበራት ያለባቸውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ በባንክ ሂሳብ ገቢ አድርገው በሚያቀርቡት የባንክ ዲፖዚት እስሊፕ ገንዘቡ ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ የገቢ ደረሰኝ ይቆርጣል እንዲሁም ተገቢውን የሂሳብ ምዝገባ በማድረግ ሂሳቡን ያቀናንሳል።

7.5. ወደ ግል የተዛወሩ የልማት ድርጅቶች ወይም አክሲዮን ማህበራት የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር እና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ዕዳ በውሉ ላይ በተቀመጠው ጊዜ ካልከፈሉ በውሉ የተመለከተውን ወለድ እና ቅጣት ጨምረው እንዲከፍሉ ይደረጋል።

ክፍል አምስት

8. የፕራይቬታይዜሽን ሽያጭ የክፍያ አሰባሰብ፣ ባንክ ገቢ የማድረግና እና ሪፖርት አቀራረብ ዝርዝር አሠራር

8.1. ገዢ መክፈል ያለበት ሂሳብ መሰላት ያለበት በፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ይሆናል።

8.2. ማንኛውንም ዓይነት ክፍያ ሰነዶች ከባለጉዳዩ መቀበል ያለባቸው ገንዘብ ያገሮች ብቻ ይሆናሉ።

8.3. ከፋዩ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርግ በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት እራሱ በቀጥታ በተገለጸው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ አድርጎ የባንክ ዲፖዚት እስሊፕ ይዞ ከመጣ የሚሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ገንዘብ ያዥ በቅድሚያ ብሄራዊ ባንክ በመሄድ ገንዘቡ በትክክል ወደ ባንክ ሂሳቡ ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ ለከፋዩ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

8.4. ከፋዩ የክፍያ ሲ.ፒ.ኦ ወይም ቼክ በአካል ይዞ ከመጣ የገቢ ደረሰኝ ከመቆረጡ በፊት ገንዘብ ያዥ የቀረበውን ቼክ ወይም ሲ.ፒ.ኦ ወደ ተዘጋጀበት ባንክ በመሄድ በክፍያ ሰነዱ ላይ የፈረሙ ኃላፊዎችን በመጠየቅና በማስፈረም ሰነዱን ማረጋገጥ አለበት።

8.5. ገንዘብ ያዥ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠውን ቼክ ወይም ሲ.ፒ.ኦ ብሄራዊ ባንክ በመውሰድ እና ገቢ በማድረግ ገቢ የሆነበትን የባንክ ዲፖዚት እስሊፕ ዋናውን ኮፒ ለከፋዩ በመስጠት ኮፒውን ለዳይሬክቶሬቱ ያስረክባል።

8.6. የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ በመያዝ ገንዘቡ ገቢ መሆኑን ብሄራዊ ባንክ በመሄድ ካረጋገጠ በኋላ በከፋዩ ድርጅት ስም የገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት ለከፋዩ ይሰጣል።

8.7. ለጨረታ ማስከበሪያ የሚቀርቡ የጨረታ ማስከበሪያ ሰነዶች ከጨረታ ከሚቱው በማስታወሻ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በአደራ እንዲቀመጡ ሲቀርቡ ገንዘብ ያገዥ የሰነዱን ትክክለኛነት ከተጻፈበት ባንክ በመሄድና በማረጋገጥ በአደራ መቀበያ ደረሰኝ ወይም የአደራ ሰነዱን ለመቀበያነት በተዘጋጀው ቅጽ ላይ መዝግቦ በመቀበል በካዝና ውስጥ እንዲቀመጥ ያደርጋል፣ የሰነዱ ትክክለኛ ኮፒ በዕለቱ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ይሰጣል።

8.8. ገንዘብ ያዥ የሚሰበሰቡ ክፍያዎችን በየቀኑ ለዚሁ ዓላማ በተከፈተው የመንግሥት ሂሳብ ገቢ ማድረግ አለበት።

8.9. የጨረታ ማስከበሪያ ሠነዶች አስፈላጊው ክትትል እየተደረገባቸው የጊዜ ገደባቸው ከማለቁ ከ15 የስራ ቀናት በፊት ፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ በጽሁፍ ሪፖርት ያደረጋል።

8.10. ገንዘብ ያዥ ከልማት ድርጅቶች ሽያጭ፣ ከሊዝ እና ከሌሎች የሚሰበሰቡ የገቢ ሰነዶች ላይ አጠራጣሪ ሁኔታ ከተመለከተ ወዲያውኑ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

8.11. ገንዘብ ያዥ የድርጅቶችን ሽያጭና ሊዝ ክፍያ በሚመለከት የሚቀበለው /የምትቀበለው/ ቼክና ሲ.ፒ.ኦ ብሔራዊ ባንክ ገቢ ከመደረጉ በፊት የክፍያ ሰነዱ ወደ ተሰጠበት ባንክ በመሄድ ትክክለኛ መሆኑ መረጋገጥ ስላለበት እና ለዚህም ስራ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚያስፈልግ ከከፋዮች ገንዘብ የሚሰበሰብበት በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 2:30 — 6:30 እንዲሁም ከሰዓት 7:30 — 9:00 ድረስ በስራ ቀናት ብቻ ይሆናል።

8.12. ገንዘብ ያዦች ከላይ በተጠቀሱት ሰዓታት የሰበሰቡትን ገንዘብ፣ ሲ.ፒ.ኦ ወይም ቼክ ከ9-10 ሰዓት ባለው ጊዜ በየባንኩቹ በመዘዋወር ትክክለኛነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ወደ ብሔራዊ ባንክ በመሄድ ገቢ ማድረግ ይገባቸዋል።

8.13. የልማት ድርጅቶችን የጨረታ ሰነድ የሚገዙ ባለሃብቶችና ተቋማት የሚያቀርቧቸው የጨረታ ማስከበሪያ ሠነዶች ከጨረታው አሸናፊ ጋር ውለታ እንደተፈረመ የሚመለስ በመሆኑ እስከዚያው ድረስ ገንዘብ ያዦች በአደራ መቀበያ ደረሰኝ ተረክበው አስቀምጠው ከኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ሰነዶቹ ለተሸናፊዎች እንዲመለሱ ማስታወሻ ሲቀርብ ወዲያውኑ እንዲመለሱ ማድረግ አለባቸው። አሸናፊው ድርጅትም ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ወደ ሽያጩ ሂሳብ እንዲታሰብለት ከጠየቀ በተመሳሳይ ከኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ማስታወሻ ሲቀርብ ገቢ ሊደረግ ይችላል።

8.14. በተራ ቁጥር 8.13 በተገለጸው አግባብ ተመላሽ የሚደረገው የጨረታ ማስከበሪያ ሠነድ የሚመለሰው ያስያዘው ባለሃብት ወይም ህጋዊ ወኪል በአካል ሲቀርብ ብቻ ይሆናል።

8.15. በአደራ የተቀመጡ ቼኮች እና ሲ.ፒ.ኦዎች ከኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ወደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የባንክ አከውንት እንዲገባ ሲወሰን ቀናቸው ከማለፉ ቢያንስ ከ5 የስራ ቀናት በፊት ገንዘብ ያዥ ወደ ባንክ በመውሰድ ገቢ ማድረግ አለበት።

8.16. የልማት ድርጅቶችን ሽያጭ፣ ሊዝ፣ የርክክብ ልዩነት፣ የመንግስት ትርፍ ድርሻ፣ እና የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ብድር ወይም ሌላ ተዛማጅ ክፍያ ሁኔታን በተመለከተ የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ቢያንስ በየወሩ ለሚኒስትሯ/ሩ ጽሕፈት ቤትና ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ በጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባል።

9. የሊዝ ክፍያ አሰባሰብ

9.1. በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ አማካኝነት የሊዝ ውሎች ኮፒ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት፣ ለኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት፣ ለህግ ዳይሬክቶሬት፣ ለኦዲት ዳይሬክቶሬት እና ለሪከርድ እና ለዶክመንቴሽን በወቅቱ መስጠት አለባቸው።

9.2. የሊዝ ክፍያ አሰባሰብ የሚፈጸመው በውሉ መሰረት ይሆናል።

9.3. በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ አማካኝነት ከሊዝ ጋር በተያያዘ የሚወሰኑ ውሳኔዎች፣ የሚደረጉ ማሻሻያዎች እና ከክፍያ ጋር በተያያዘ የሚደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች እንዲሁም የሊዝ ስምምነቱ በሚቋረጥበት ጊዜ በወቅቱ ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት እና ለኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት፣ ለህግ ዳይሬክቶሬት እና ለኦዲት ዳይሬክቶሬት ሊገለጽላቸው ይገባል። ክፍል- ስድስት

10. ልዩ ልዩ የሥራ ኃላፊነቶች

10.1. ከቀሪ ክፍያ ነጻ ስለ መሆን ማረጋገጫ ስለ መስጠት እና ሪፖርት ስለማቅረብ

ሀ. ከቀሪ ክፍያ ነጻ የመሆን ማረጋገጫ እና የባለቤትነት ለውጥ እንዲደረግ ለገገር በጽሁፍ የሚሰጠው በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ በኩል ሲሆን ይህም ሂሳቡን በአግባቡ በማስላት ገገር ያለበትን ክፍያ በሙሉ ስለመፈጸሙ በፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት የመጨረሻ ማጣራት ከተደረገና ይህን የሚያረጋግጥ ማስታወሻ ለዘርፉ ከቀረበ በኋላ ብቻ ይሆናል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ለ. የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በተራዘመ ክፍያ የተሸጡ ወይም በሊዝ የተላለፉ ድርጅቶችን ሂሳብ በተመለከተ በየሩብ ዓመቱ መጀመሪያ የነበረውን ቀሪ ተሰብሳቢ ባላንስ፣ በሩብ ዓመቱ የተሰበሰበውን ገንዘብ መጠን፣ መሰብሰብ የነበረበትን የገንዘብ ልክ እንዲሁም የወለድና የቅጣቱን መጠን በዝርዝር በማስላት ለሚኒስትር ጽሕፈት ቤት እና ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

10.2. ልዩ ልዩ ኃላፊነቶች

ሀ. የህግ ዳይሬክቶሬት ባልተፈጸመ የውል ግዴታ ላይ በፍርድ ቤት ክርክር ተደርጎ የተሰጠውን የፍርድ ቤት ውሳኔ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሚኒስተር እና ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ፤ ለኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

ለ. ማንኛውም ወደግል ከተዛወሩ ድርጅቶች የሚፈለግ ክፍያ እንዲሰበሰብ የማድረግ ሥራ በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ የበላይ ኃላፊነት ይከናወናል፡፡

ሐ. ክፍያ ሲፈፀም የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ወዲያውኑ የደረሰኞቹን ኮፒ ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ በቋሚነት መላክ ይኖርበታል፡፡

መ. ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ ወይም በአፈፃፀም ሂደት ላይ እያለ ክፍያ የፈፀሙ ገዢዎች ሲኖሩ የሕግ ዳይሬክቶሬት ወይም የኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት እንደአስፈላጊነቱ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት የፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት ክፍያው እንደተፈፀመ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

ሠ. የህግ ዳይሬክቶሬት ቀሪ ዕዳ በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት ወደ ሕግ የተመሩ ጉዳዮችን የፍርድ ሂደት ያለበትን ደረጃ ወር በገባ በመጀሪያው ሳምንት ለሚኒስትሯ/ሩ እና ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

ረ. የኦዲት ዳይሬክቶሬት የልማት ድርጅቶች ወይም አክሲዮን ማህበራት ርክክብ ተጠናቆ ኦፕሬሽን የተላለፈበትን ቀን የሚገልጽ ደብዳቤ ለኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ እና ለፋይናንስና በጀት ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ይልካል፡፡

ሰ. የህግ ዳይሬክቶሬት ከእዳ ነፃ ማስረጃ ለገገሮች ከተሰጠም በኋላ ቢሆን በሂሳብ ስሌት ስህተት ምክንያት ያልተከፈለ ቀሪ ገንዘብ መኖሩን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ካረጋገጠና ሂሳቡንም በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፎ ካቀረበ ክፍያውን የመጠየቅ መብት እንደሚኖረው በመጀመሪያው የውሰታ ሰነድ ሁል ጊዜም እንዲካተት ያደርጋል፡፡

ሸ. የህግ ዳይሬክቶሬት የልማት ድርጅቶችን ወይም አክሲዮን ማህበራትን የገዙ ባለሃብቶች ከክፍያ ጋር በተያያዘ የገቡትን ውል ተፈጻሚ ባያደርጉ አንድ አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጉዳያቸው ወደ ሕግ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

ክፍል- ዘጠኝ

11. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴት ጾታንም ይጨምራል፡፡

12. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ጉዳዮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ እና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

13. መመሪያውን ስለማሻሻል

ማናቸውም በዚህ መመሪያ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ለሚኒስቴሯ/ሩ ቀርቦ ፀድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ካልተፈቀደ በስተቀር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጳጉሜ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ 1 ቀን 2008 ዓ.ም.

ደሚቱ ሀምቢሣ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር